መብቶችዎን ይወቁ

ለልጅዎ የማኅበራዊ ዋስትና ችሎት (SSI) እንዴት መዘጋጀት እንደሚችሉ

1 የልጅዎን የማህበራዊ ዋስትና ችሎት ሥራዎች ጽሕፈት ቤት (Office of Hearing Operations, OHO) ፋይል ይገምግሙ

OHO በልጅዎ ፋይል ውስጥ ያሉትን ከሕክምና እና ከአካል ጉዳት ጋር የተያያዙ ሁሉንም መዝገቦች ለእርስዎ መላክ አለበት፣ ይህም ሲዲን በፖስታ በመላክ ወይም የኢሜይል አድራሻ ካለዎት፣ በይለፍ ቃል በተጠበቀ ኢሜይል በኩል በመላክ ነው። ልጅዎ የችሎት ቀን እስኪመደብለት ድረስ መዝገቦቹ ካልደረሱዎት፣ ወደ OHO ይደውሉ እና እነሱን ይጠይቁ፦ (866) 414-6259።

2 የልጅዎን መዝገቦች ከሐኪሞቹ እና ከትምህርት ቤቱ ይጠይቁ

ከልጅዎ ሐኪሞች፣ ቴራፒስት፣ የጉዳይ ሠራተኛ እና ትምህርት ቤት የቅርብ ጊዜ (ያለፉት 2-3 ዓመታት) መዝገቦችን መጠየቅ አለብዎት።

- የልጅዎን የቀድሞ እና የአሁኑን የሕክምና አቅራቢዎችን (ሆስፒታሎችን ጨምሮ) የሕክምና እና የአእምሮ ጤና መዝገቦችን ይጠይቁ። ይህም የላብራቶሪ ምርመራ ውጤቶችን (እንደ የደም ምርመራዎች) እና የምስል ምርመራ ውጤቶችን (እንደ X-rays (ኤክስሬይዎች) እና MRIs (ኤምአርአይዎች) ያካትታል። የልጅዎን ምርመራ፣ ምልክቶች፣ መድሃኒቶች እና በመሥራት ችሎታው ላይ ያሉ ችግሮችን የሚገልጹ ደብዳቤዎችን ወይም ሪፖርቶችን መጠየቅ አለብዎት።
- የልጅዎን የትምህርት መዝገቦች፣ ይህም እንደ IEPዎች፣ የመገኘት እና የዲሲፕሊን መዝገቦችን እንዲሁም የማንኛውንም ፈተና ውጤቶችን ከልጅዎ ትምህርት ቤት ይጠይቁ። የልጅዎን መምህራን የመምህራንን መጠይቅ እንዲሞሉ መጠየቅ ይችላሉ፦ www.ssa.gov/forms/ssa-5665-bk.pdf።
- እርስዎ ወይም ልጅዎን የሚያውቁ ሌሎች ሰዎች፣ ስለ ልጅዎ የተግባር ሪፖርቶችን መሙላት ይችላሉ። ለተለያዩ ዕድሜዎች የተለያዩ የተግባር ሪፖርቶች አሉ፣ ሁሉም በhttps://www.ssa.gov/forms/ ላይ ይገኛሉ፦
  - ከልደት እስከ 1 ዓመት ዕድሜ፦ ቅጽ SSA-3375
  - ዕድሜ 1–2፦ ቅጽ SSA-3376
  - ዕድሜ 3-5፦ ቅጽ SSA-3377
  - ዕድሜ 6–11፦ ቅጽ SSA-3378
  - ዕድሜ 12-17፦ ቅጽ SSA-3379
- እንዲሁም መዝገቦችን ለማግኘት እርዳታ ለመጠየቅ ወደ OHO መደወል ይችላሉ፦ (866) 414-6259።

3 ከችሎቱ ቢያንስ ከ5 የሥራ ቀናት በፊት ለOHO የህክምና እና የትምህርት መዝገቦችን መስጠት

የሁሉንም መዝገቦች ቅጂ ለራስዎ ይያዙ እና ከዚያም መዝገቦቹን ወደ OHO ይላኩ ወይም በእጅ ያስረክቡ። OHO ሁሉንም መዝገቦች ቢያንስ ከችሎቱ ከ5 የሥራ ቀናት በፊት መቀበል አለበት። መዝገቦቹን በጊዜው ማግኘት ካልቻሉ፣ አስፈላጊ መዝገቦቹን ለማግኘት ሞክረው እንደነበር ነገር ግን ማግኘት እንዳልቻሉ ለማስረዳት ከችሎቱ ቢያንስ ከ5 ቀናት በፊት ለዳኛው ማሳወቅ አለብዎት። ችሎቱ ከመካሄዱ በፊት ወይም በችሎቱ ጊዜ መዝገቦቹን ለማግኘት የዳኛውን እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ፣ ነገር ግን ዳኛው ጥያቄዎን ላይቀበል ይችላል።

4 ስለ ልጅዎ የአካል እና/ወይም የአእምሮ ሁኔታዎች ለመናገር ይዘጋጁ

ልጅዎ ስለ ሁኔታዎቹ በራሱ ማብራራት ከቻለ፣ ምስክርነት እንዲሰጥ ሊጠበቅ ይችላል። በችሎቱ ላይ እርስዎ (እና ልጅዎ፣ ምስክርነት መስጠት ከቻለ) የአካል እና/ወይም የአእምሮ ሁኔታዎቹ በየቀኑ ምን ያህል በተደጋጋሚ እና ምን ያህል ከባድ እንደሆኑ፣ ይህም ማንኛውንም ህመም ጨምሮ፣ ማብራራት አለባችሁ። እንዲሁም የልጅዎ ሁኔታ የሚከተሉትን የማድረግ ችሎታዎቹ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድርዝርዝር ማብራሪያዎችን ያብራሩ፦

1. አዳዲስ መረጃዎች ላይ ማተኮር እና መማር
2. ትኩረት ማድረግ እና ሥራዎችን ማጠናቀቅ
3. ከሌሎች ጋር መነጋገር እና መስማማት
4. መዘዋወር እቃዎችን ማንሳት
5. ስሜታዊ እና አካላዊ ፍላጎቶቻቸውን ማሟላት
6. አጠቃላይ ጤናን መጠበቅ

ልጅዎ ከእርስዎ ጋር ወደ ችሎቱ ለመምጣት የሚያስችል ዕድሜ ካለው፣ ልጅዎ በሌለበት ስለ ልጅዎ የአካል ጉዳት መናገር እንዲችሉ ዳኛውን ይጠይቁ። ሚስጥራዊ ስለሆኑ ጉዳዮች በግልጽ ሁኔታ ለመነጋገር ምቾት መሰማትዎ አስፈላጊ ነገር ነው። እንደ ልጅዎ ዕድሜ ሁኔታ፣ እርስዎ እና ልጅዎ ወደ ችሎቱ ሲሄዱ አብሮዎት የሚሄድ ሰው ቢኖር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፤ ይህም እርስዎ ምስክርነት በሚሰጡበት ጊዜ ከችሎቱ ውጭ ከልጅዎ ጋር ለመቀመጥ የሚችል ሰው እንዲኖር ያደርጋል።

ልጅዎ የአደንዛዥ ዕጽ አጠቃቀም ታሪክ ካለው፣ የአደንዛዥ ዕጽ አጠቃቀሙ የአካላዊ ወይም የአእምሮ ጤና ሁኔታው ከተከሰተ በኋላ እንደጀመረ ለማስረዳት ዝግጁ ይሁኑ።